# <u>እምነት እና ጽናት</u>

**ለተገኘ ሞገስ** መታሰቢያ (ከተስፋሁን አረጋይ ከአትላንታ )

መቼ ጎጆ ላቁም ንብረትስ ላፍራ አለ

መቼ ልቡ ካደ መቼ ክንዱ ዛለ

ከአላማው ተዛንፎስ መች ጓዶቹን ካደ

በእምነቱ እንደጸና ከቃሉ ጋር ሄደ።

ስደት እና ችግር ቃሉን አልቀሙትም

በአካሉ ነው እንጅ በአላማው አይሞትም

ጥቅምእና ንብረትን እንደተጸየፈ

ቃሉን ያከበረ በዓላማው የጸና አንድ ሰው አረፈ

ምነው ጓድ ተገኘ

ምነው ጋሼ ተገኘ

ምነው አባ ተገኘ እንደወጣህ ቀረህ

ለአገር የሚያበቃ ትልቅ ህልም እያለህ

ወገንክን ሳትከዳ በምቾት ተታለህ

አገርክን ስትናፍቅ የሰው አገር በላህ?

አባዬ

አባዬ

አባዬ እንደወጣህ እንዴት ትቀራለህ

የሰው አገር አፈር እንዴት ትበላለህ?

ቃልክን እንዳከበርክ ስጋህ ተሸነፈ

ጀግናው ታጋይ ተብሎ ስምህ ግን ገዘፈ

ጊዜው መጥፎ ሆኖ በክብር ባንሸኝህ

ተገኘ አንረሳህም ያባ ትልቅ ልጅ ነህ

በአገር ጽሃይ ጠፍቶ ስለጨለመበት

እንደወጣ ቀረ ደምመና ሆኖበት

ብላችሁ መስከሩ እሱን የምታውቁ

እምነት ጽናቱን ግን ዘላለም አድንቁ

ሃዘኑም ሃዘን ነው አገር ወዳድ ይስማ

አገሬ ልጅ አጣች ስለ እርስዋ እሚደማ

ስለ ዴሞክራሲ መፈክር  ሲያነሳ

ለፍትህ ለኩልነት ሲወድቅ ሲነሳ

ተገኝ ለአገሩ እንጅ መች ለራሱ ሳሳ

ለህዝብዋ ሲታገል መብቱ እንዲከበር

እራሱን እረስቶ የኖረ ስለ ሃገር

አልሞተም ይህ ጀግና አካሉ ቢቀበር

ይመስክር  ኢሕአፓ ታሪኩም ይነገር

ጥቅምእና ንብረትን እንደተጸየፈ

ቃሉን ያከበረ በዓላማው የጸና አንድ ሰው አረፈ

ሀብት አለኝ ልጅ አለኝ ብሎ ከመኩራራት

መቅናትስ ባንተ ነው እምነት እና ጽናት።

Tesfahun Aregay